

# የጳውሎስ አገልግሎት በቆሮንቶስ


“ጌታም ሌሊት
በራእይ
ጳውሎስን፦ እኔ
ከአንተ ጋር ነኝ፥
ማንም ክፉ
ሊያደርግብህ
የሚነሣብህ የለምና
አትፍራ፥ ነገር ግን
ተናገር ዝምም
አትበል፤ በዚህ
ከተማ ብዙ ሕዝብ
አሉኝና አለው ”
(የሐዋ 18፡9, 10)

ከሮሜ ሰዎች መልዕክት ቀጥሎ ለቆሮንቶስ ሰዎች የተፃፉት ሁለቱ መልዕክቶች ረጅም የሆኑ ደብዳቤዎች ናቸው።

ለእኛ የተረፉት ሁለቱ ደብዳቤዎች የተፃፉት በጥቂት ሳምንታት ልዩነት ውስጥ ነበር። በወንድሞች መካከል በሚፈጠር አለመስማማት ምክንያት የሚመጡ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መፍታት የሚያስችሉ ተግባራዊ ምክሮችን በእነዚህ ደብዳቤዎች ውስጥ እናገኛለን።

መልዕክታቸውን በትክክል ለመረዳት በመጀመሪያ የተፃፉበትን አውድ ማወቅ አለብን።





- የጳውሎስ ጥሪ
- ጉዞ ወደ ቆሮንቶስ
- የቆሮንቶስ ከተማ
- የቆሮንቶስ ሰዎች
- የቆሮንቶስ ሰዎች መልዕክት



# የጳውሎስ ጥሪ

"በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ..." (ገላትያ 1:1)

ኢየሱስ ከመረጣቸው ከአስራ ሁለቱ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ማትያስ (የሐዋ 1:26)፣ በርናባስ (የሐዋ 14:4)፣ ያዕቆብ እና ጳውሎስ ያሉ ሐዋርያትን ይገልጽልናል (1 ቆሮ 15:7-9)።



| | |
|---|---|
| ጳውሎስ ሐዋርያ የሆነው እንዴት ነው? | በኢየሱስ ምርጫ (ገላ 1:1) |
| የተመረጠው መቼ ነው? | በእናቱ ማህፀን እያለ (ገላ 1:15) |
| የተጠራው መቼ ነው? | በደማስቆ መንገድ ላይ (የሐዋ 22:6-7) |
| ሐዋርያነቱ ለማን ነበር? | የአሕዛብ ሐዋርያ ነው (ገላ 2:9) |



ጳውሎስ ከተጠራበት ጊዜ አንስቶ ሕይወቱ ኢየሱስን ማዕከል ያደረገ ነበር። ስለ ኢየሱስ የሚያስብ፣ የሚናገርና ላገኘው ሰው ሁሉ ስለ ኢየሱስ የሚመሰክር ነበር።

በዚህም ምክንያት ወደ ቆሮንቶስ ለመጀመሪያ ከመጣበት ጊዜ አንስቶ ኢየሱስ የመልዕክቱ ማዕከል ነበር (1ቆሮ 2:2)።

# ጉዞ ወደ ቆሮንቶስ

**“ከዚህም በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ መጣ።” (የሐዋ 18:1)**



ጳውሎስ በሁለተኛው የተልዕኮ ጉዞው ወደ አውሮፓ እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ መርቶት ነበር (የሐዋ 16:6-10)። ከዚያም በፊልጵስዩስ (የሐዋ 16:12፣ 38-39) በተሰሎንቄ (የሐዋ 17:1, 5, 9-10) እና በቤርያ (የሐዋ 17:13-14) ከተሞች እየዞረ ተሰደደ።



በአቴና ለአይሁዶች በሙክራብ ውስጥ ለአሕዛብ ደግሞ በገበያ ከሰበከ በኋላ በአርዮስ ፋጎስ እንዲሰብክ ተጠራ (የሐዋ 17:16-21)። በዚያም አስገራሚ ንግግርን ቢናገርም ጥቂቶች ብቻ ኢየሱስን ተቀበሉ (የሐዋ 17:34)።

ጳውሎስ ከዚያ ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ በመሄድ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር በመሆን ድንኳን ሲሰፋ ቆየ (የሐዋ 18:1-3)።



እንደ ልማዱም በሙክራብ ለአይሁድ ይሰብክ ጀመር፤ ቀጥሎም ለአሕዛብ ሰበከ (የሐዋ 18:4-8)። ከአቴናው “ያልተሳካ” ጥረት በኋላ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቆይታው የሰውን ጥበብ ሳይሆን “ኢየሱስ ክርስቶስንና የእርሱን መስቀል” ብቻ ለመስበክ ወሰነ (1 ቆሮ 2:2)።



# የቆሮንቶስ ከተማ

“መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ ...” (1 ቆሮንቶስ 8:5)



በ146 ዓመተ ዓለም ቆሮንቶስ በሮም ተደምስሳ ነበር። ቀጥሎም ጁሊየስ ቄሳር በ46 ዓመተ ዓለም የተለያዩ ባለሙያዎችና ነፃ ሰዎችን በዚያ እንዲሰፍሩ ልኮ ነበር። በመጨረሻም ከተማዋ በ 44 ዓመተ ዓለም ሙሉ በሙሉ አገገመች። ጳውሎስ ከተማዋን በጎበኛት ጊዜ ዋና የንግድ ማዕከል ለመሆን በቅታ ነበር።

የቆሮንቶስ ከተማ ተፈላጊነት በመገኛዋ ላይ ያጠነነ ሲሆን ባህርን በማቋረጥ ሁለት አገራትን የምታገናኝ ሾጣጣ መሬት ናት። በቀኝና በግራ ደግሞ ሁለ ዋና የንግድ ወደቦች አሉባት። በቆሮንቶስ ባህረ ሰላጤ በኩል ለኬዩም ስትገኝ በሳሮኒክ ባህረ ሰላጤ በኩል ደግሞ ክንክራኦስ አለች።



ጳውሎስም በሙያው በድንኳን ሰፊነት ተሰማርቶ ነበር። ነገር ግን ከአቴና ጋር የሚስተካከለው የቆሮንቶስ ሀብት በርካታ መዘዞች ነበሩት።



ጣዖት አምልኮና መዳራት ከተማይቱን የሞላና ባህሏን የተቆጣጠረ ነበር። የጳውሎስ መልዕክት ለቆሮንቶስ ሰዎች ዋና ዓላማው ወደ ቤተክርስቲያን እየሾለኩ የነበሩትን እነዚህን ችግሮች ለማጥፋት ነበር።



# የቆሮንቶስ ሰዎች

"ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን፡- እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ...፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤..." (የሐዋ 18:9)





የቆሮንቶስ አይሁዶች የጳውሎስን መልዕክት አልተቀበሉትም፤ ሙክራባቸውንም እንዲለቅ አስገደዱት። በዚህም ሳቢያ ከሙክራቡ አቅራቢያ ባለ ቤት ውስጥ አሕዛብን መገናኘት ጀመረ (የሐዋ 18:4-7)።

"በአሕዛብ ዘንድ የተመለከተው ዝቅጠት ብሎም ከአይሁድ ያጋጠመው ጥላቻና ስድብ ታላቅ የመንፈስ ሀዘን አስከትሎበት ነበር። በአካባቢው ባገኘው ነገር ቤተክርስቲያንን የመትከል ጥበብን የተጠራጠረበት ጊዜ ነበር"

(EGW The Acts of the Apostle ገጽ፣ 250)።



ኢየሱስ በዚያን ሰዓት በሌሊት ህልም ተገልጦ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሰዎች የጀመረውን ስራ እንዲቀጥል አበረታታው፤ መልዕክቱንም የሚቀበሉት ብዙዎች እንደሚኖሩ አረጋገጠለት (የሐዋ 18:9-10)።



በዚህ ራዕይ ከተበረታታ በኋላ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለአንድ አመት ተኩል ቆየ (የሐዋ 18:11)። በመጨረሻም አይሁድ ጳውሎስን ወደ ፍርድ ወንበር አቀረቡት (የሐዋ 18:12-13)። ጳውሎስ ከቆሮንቶስ በሄደ ጊዜ ግን አንድ ትልቅ ቤተክርስቲያን ተቋቁሞ ነበር (የሐዋ 18:18)።

# የቆሮንቶስ ሰዎች መልዕክት

“ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና።” (1 ቆሮንቶስ 1:11)

## 1 ቆሮንቶስ 1-6

እንደ መከፋፈል፣ መዳራት፣ ክርክርና ግልሙትና የመሳሰሉት ችግሮች በቤተክርስቲያን እንዳሉ ጳውሎስ ከቀሎዔ ስለሰማ እነዚህን ይገስፃል።





## 1 ቆሮንቶስ 7-16

የቀሎዔ ቤተሰብ እንደ ትዳር፣ ፍቺ፣ ጃንደረባነት፣ ለጣዖት የተሰዋ ምግብ፣ የአምልኮ ስነ-ስርዓት፣ የመንፈስ ስጦታዎችን አጠቃቀም እና ትንሳኤ የመሳሰሉ በርካታ ጥያቄዎችን የያዘ ደብዳቤ ጳውሎስ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ልከውለት ነበር።



## 2 ቆሮንቶስ

ምንም እንኳን ጳውሎስ ተጨማሪ መልዕክቶችን ከእነዚህ በፊት ወይም በመካከል ጽፎ ቢሆንም ይህ ተጠብቆ የቆየው ሁለተኛው ደብዳቤ ነው። የቆሮንቶስ ሰዎች አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታት የሄዱበትን መንገድ እያመሰገነ ደግሞ ዓለምን በወንጌል መነጽር እንዲያዩና የከበባቸውን የአኗኗር ባህል እንዲቋቋሙ ይመክራቸዋል።



“የእግዚአብሔር መልዕክተኞች በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ባለው ክፋት፣ የፍርድ ጠማማነትና ዝቅጠት የመዳንን የምስራች ለማወጅ ሲሰሩ እንዲጋፈጧቸው የሚገቡ ናቸውና በእነዚህ ሊያዝኑና ተስፋ ሊቆርጡ አይገባም። ጌታ እንዲህ ያለውን ማንኛውንም ሰራተኛ ሊያጽናና ለሐዋርያው ጳውሎስ በረከሰው በቆሮንቶስ በነበረ ጊዜ የተናገረውን መልዕክት እንዲህ ብሎ ይደግምለታል: “ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን፦ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው።” የሐዋ 18:9፣10... [...] የትኛውም ከተማ ምንም እንኳን በግፍና በወንጀል ቢሞላ ትክክለኛውን ትምህርት ካገኙ ጌታን ለመከተል የሚበቁ ብዙዎች አሉ። እንዲሁም ሺዎች የሚያድነው እውነት ሊደርሳቸውና ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው ሊቀበሉት ይችላሉ።”

EGW (Prophets and Kings, p. 277)